# መሰናበቻ መሰናበቻ፥ ሦስት ቀን ብቻ

**ከጌታቸው ኃይሌ**

ጊዜው በሚያሳስብ ፍጥነት ሮጠ፡፡ የዚህ አጭር ድርሰት ርእስ መነሻ የሆነው ኅዳር 13 ቀን አዲስ አበባ ላይ በተካሄደው ታላቅ የሩጫ እሽቅድድም የተሳተፉ ሯጮች ያስሰሙት ሆታ ነው፡፡ የተሰማው ሆታው የሚለው "መሰናበቻ መሰናበቻ፥ ስድስት ወር ብቻ" ነበር፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ቀኑ ሳይደርስ የማሰናበቻው ድግስ እንዲሟላ ደጋግሜ አሳሰቤ ነበር፡፡ ጊዜው በሚያሡጋ ፍጥነት ሮጦ አለቀ፡፡ አሁን አቶ መለስ ዜናዊን ከነአሰሱ ከነገሡሡ ለማሰናበት የቀረው ጊዜ ሦስት ቀን ብቻ ነው፡፡ እኔም ሆንኩ ሌሎች ብዙዎች፥ በተለየም ተቃዋሚዎች፥ በተደጋጋሚ ስላሳሰቡ፥ በፍጥነት በርሮ ባለፈው የስድስት ወር ጊዜ ውስጥ አስተማማኝ የመሰነባበቻ ዝግጅት እንደተደረገ ሙሉ ተስፋ አለኝ፡፡ ሯጮቹ "መሰናበቻ መሰናበቻ፥ ስድስት ወር ብቻ" ሲሉ፥ "የትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር ሰዎች በጉልበትና በማጭበርበር በኢትዮጵያ ላይ የዘረጉትን የትግራይ የጭቆናና የሥቃይ አገዛዝ ከስድስት ወር በኋላ በሚደረገው የግንቦት 2002 ዓ.ም. ምርጫ ከሕዝብ ቤተ መንግሥት ጠቅልለው እንዲወጡ በሩን እናሳያቸዋለን" ማለታቸው ነበር፡፡ ለዚህ ታሪካዊ በዓል የሚያስፈልገው ዝግጅት "ሠርገኛ መጣ ብሎ" መርበድበድ ሳይሆን በማያዳግም ሁኔታ በሙሉ ኀይል ለመገፍተር ታጥቆ መነሣት ነው፡፡

**ታይቶ የማይታወቅ ጠላት፤**

ኢትዮጵያ ታሪኳን እንደምናውቀው ከሆነ እንደዛሬው ያለ ጠላት ተነሥቶባት፥ እንደዛሬው ያለ የጠላት ማስወገጃ ዘዴ ገጥሚት አያውቅም፡፡ ስለዚህ ነው ምስጢሩ የገባቸው አስተዋዮች "ጠላትህን ዕወቅ፥ ማሸነፊያውን እንድታውቅ" የሚሉት፡፡ አሁን ኢትዮጵያን የሚገዟት ሰዎች የኢትዮጵያ ጠላቶች መሆናቸውን ከሚሡሩት ብንጠረጥርም፥ እንደዛሬው ጊዜ ወገግ ብሎ አልታየንም ነበር፡፡ በመሳሳት አብረዋቸው የነበሩ ሰዎች አሁን እየራቋቸው ሄደው፥ የትግራይ ወያኔዎች የተፀነሱት ኢትዮጵያን ወይ ለመግዛት ወይ ለማጥፋት መሆኑን የዓይንና የጆሮ ምስክርነታቸውን በመጽሐፍ መልክ እያቀረቡልን ነው፡፡ አቶ መለስም ቢሆን፥ "ኢትዮጵያ አትከፋፈልም" የሚሉትን ተቃዋሚዎች የሚፈርጃቸው በጠላትነት እንደሆነ ያልሰማ ያለ አይመስለኝም፡፡ እነዚህ ሰዎች እኅቶቻችንና ወንድሞቻችን መሆናቸው እስከዛሬ ያሳሳተን አንሶ አሁንም እንዳያሳስተን እንጠንቀቅ፤ መጽሐፋችን "ወሰብአ ቤቱ ይፃረሮ ለሰብእ" (ሰውን ጠላቱ የሚሆንበት የገዛ ቤቱ ሰው ነው) የሚለውን አንርሳ፡፡ አገሪቱ እንደዛሬው ያለ ጠላት ተነሥቶባት አያውቅም የሚባለው ስለዚህ ነው፡፡

እነዚህ የኢትዮጵያ ጠላቶች የሰጡንን ምርጫ ልብ እንበለው፤ <u>አርፎ መገዛት</u> ወይም <u>ሀገር አልባ መሆን፡፡</u> ዘላለም በነፃነት የኖረ ኩሩ ኢትዮጵያዊ አርፎ መገዛትን እንደማይቀበል እኛ ብቻ ሳንሆን እነሱም ያውቁታል፡፡ ታዲያ ከዐወቁት እንዴት ሊገዙን ደፈሩ? መልሳቸው ቀላል ነው፤ አንድ ሕዝብ ላለመገዛት አቅም የሚኖረው አንድነት ያጣ እንደሆነ መሆኑን ያውቃሉ፡፡ የተበታተነ ሰውም ሆነ እንስሳ ለጠላት ይመቻል፡፡ ስለዚህ በአንድነት እንዳንቋቋማቸው የሚበታትን መርዝ ይረጩብናል፡፡ ለምሳሌ፥ኢትዮጵያ ወደሰማኒያ የሚጠጉ ነገዶች የሚኖሩባት ሀገር ናት፡፡ እነዚህ ነገዶች ካላወቁበት ለጠላት ምቹዎች ናቸው፡፡ በኢጣሊያ ፋሺስቶች ከተደፈርንበት አንዱ ምክንያት ነገዶቻችን ሲያጋጯቸው ስለተጋጩላቸው ነው፡፡ የትግራይ ወያኔዎች የሚገዙን በዚህ ዘዴ እየተጠቀሙ መሆኑን ልብ እንበል፡፡ መልሳችን መሆን ያለበት "እባካችሁ፥ አታጋጩን" ብሎ መለመን ሳይሆን፥ "አሻፈረን፥ አንጋጭም" ብሎ ማሳፈር ነው፡፡ ወንድሙን እንደባሪያ የሚገዛ ወርቅ ቢያፈስለት "አበጀህ፥ ግዛኝ" አይለውም፡፡ ነፃነት በገንዘብ አይተመንም፡፡

ካላወቅንበት የትግራይ ወያኔዎች ኢትዮጵያን ረግጦ ለመግዛት ከኢጣሊያ ፋሺስቶች የተሻለ ዕድል አላቸው። የኢጣሊያ ፋሺስቶች ከባሕር ማዶ የመጡ እኛን የማይመስሉ ናቸው፤ እነዚህ ግን አገር በቀል፥ ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ከመሆናቸው በላይ፥ ደም ከሚያስተፋ ደርግ ሊያላቅቁን የመጡ መስለው ታዩ። ሕዝቡ ኢትዮጵያውያንነታቸውን እያየና የደርግን ጭካኔ እያስታወሰ እነሱን እንዲያመሰግን የማይሠሩት ሥራ የለም። በሺ የሚቆጠሩ የንጹሕ ኢትዮጵያውያንን ሕይወት እያሳለፉ የምርጫ ጊዜ ሲቃረብ "ደርግ የገደለባችሁን ዘመዶቻችሁን በይፋ ቅበሩ" እያሉ በሰው ስሜት ይጫወታሉ። እንዲህ ያለውን ልገሳ እምቢ ማለት ብቻ ሳይሆን ምስጋና አለመስጠት እንኳ ያስቸግራል። አርቆ ለሚያይ ሕዝብ ግን የጠላት ልገሳ ማርም ቢሆን እንደ ሬት ይመርረዋል። በሰው ስሜት የመቀለድ ሥራቸው የባሰውን ያስጠላቸዋል እንጂ አያስመሰግናቸውም። የደርግ ሰለባዎች በአዋጁ ተጠቅመው ዘመዶቻቸን ቢቀብሩም ለጠላቶቻቸው ባለውለታነት አይሰማቸውም። እነሱ ግን በሰው ስሜት መጫወታቸው እንደሚያስጠላቸው መገመት እንኳን አልቻሉም። ቀን የሰጠው ባለጉልበት ከቀማው ሀብት ላይ ለባለቤቱ ዓሥር ብር ቢመጸውተው እንዴት ይመሰገናል!

የጭቆና ግዛታቸውን ሲጀምሩ ሌላም ማጭበርበሪያም ነበራቸው፤ አይተነው ሰምተነው የማናውቀውን የመናገርና የመጻፍ መብታችንን እንድንጠቀምበት ፈቀዱልን። ስለ ፍጹም ዲሞክራሲ ምንነት ለማያውቅ ሕዝብ ይኸን እያሳዩ የዲሞክራሲ ሥርዓት አመጣህልን ቢሉት ለአንዳንዶች እውነት መስሏል። ግን ይህን ሁሉ ያደረጉት የምዕራባውያንን ልቦና ለመሳብና ስልጣናቸውን ለመደላደል ነበር። አሁን ስልጣናቸውን ከአደላደሉ በኋላ በግላጭ የሚፈጽሙትን ወንጀል ማንም ደፍሮ አይጽፍም፤ ማንም ደፍሮ አይናገርም። ጽኑ እስራትና ሊከፍለው የማይችለው የገንዘብ መቀጮ እንዲከፍል ይፈረድበታል። ወይም ካላስገደሉት ከአገሩ ወጥቶ የጥገኝነትና የባይተዋርነት ኑሮ እንዲኖር ያደርጉታል። እነሱ ግን ሕዝቡን ቀን ከሌት በፕሮፓጋንዳ እንደደበደቡት ነው።

## እንደሌሎቹ ልንገዛችሁ እንችል ነበር፤

ባለፈው ሳምንት እንደሰማችሁት፥ አቶ መለስ ዜናዊ "እኛን ምረጡን" ለማለት በሚያደርገው ፕሮፓጋንዳ ሲናገር "እንደሌሎቹ ልንገዛችሁ እንችል ነበር" አለ። ምን ማለቱ ነው? ማንስ ጠይቆት? በነገሥታቱ አገዛዝ ዘመን እንዳሁኑ ሕዝብ በፖሊስ አልተገደለም፤ አልታሰረም። በማንኛውም ዘመን አገር አልተሸጠም። የመለስ አገዛዝ በማናቸውም ረገድ ሲታይ ከአለፉት መንግሥታት አገዛዝ ይከፋል እንጂ አይሻልም። "እንደሌሎቹ ልንገዛችሁ እንችል ነበር" ማለቱ፥ "ከፈለግን እንደነሱ ለሀገርና ለሕዝብ መቆርቆር እንችል ነበር" ማለቱ ከሆነ፥ እኛም የምንለው ይኸንኑ ነው። ለማለት የፈለገው ግን "የመናገርና የመጻፍ መብታችሁን እንድንትጠቀሙበት ፈቅደንላችኋል፤ መንግሥት መቃወም ትችላላችሁ" ነው።

የመገናኛ ብዙኃኑን ለሕዝብ እስካልለቀቀ ድረስ ምንም የፈቀደልን ነፃነት የለም። ሬትና ማር መለያቸው ጣዕማቸው እንደመሆኑ መጠን፥ በየትኛውም ሀገር የዲሞክራሲና የፋሺስት አገዛዝ መለያው መገናኛ ብዙኃን፥ በተለየም ሬዲዮና ቴሌቪዥን፥ ናቸው። እነዚህ መሣሪያዎች በመንግሥት እጅ ከሆኑ ያ መንግሥት ፋሺስታዊ ነው። በሕዝብ እጅ ከሆኑና የሕዝብ መብት ከተከበረ፥ መንግሥቱ ዲሞክራሲያዊ ነው። በሀገራችን ግን "የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን"፥ "የኢትዮጵያ ሬዲዮ" ማለት "የወያኔ ቴሌቪዥን"፥ "የወያኔ ሬዲዮ"፥ "ፋሺስቶች ሕዝብን የሚጨቁኑባቸው መሣሪያዎች" ማለት ነው። የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ ግምባር ስልጣን ከያዘ ጀምሮ የተጠቀመባቸው አንሶት ይኸው አንድ ሳምንት ሙሉ ራሱን ያገንንባቸዋል፤ አገር ወዳድ ተቃዋሚዎቹን ያጥላላባቸዋል። በመንግሥት መብት በዚህ ረገድ መጠቀም ሌብነት ነው።

ሁለተኛም በዲሞክራሲ አገዛዝ የመጻፍ መብት ጥቅሙ የመንግሥትን ወንጄል አጋልጦ ወንጀለኛውን ባለ ስልጣን ለፍርድ ለማቅረብ ነው። በመለስ ዜናዊና በግብር አበሩ በመንግሥቱ ኃይለ ማርያም አገዛዝ ይኸ እንደማይቻል ሁሉም ያውቀዋል።

የወያኔ ፋሺስቶች ከዚህ አልፈው ሄደዋል፤ የውስጡን ብቻ ሳይሆን ከውጪ የሚተላለፉትንም የሬዲዮ መልእክቶች ማፈን ጀምረዋል:: ዓለም የሚያነባቸው ድረ ገጾች ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይነበቡ የትግራይ ፋሺስቶች ዘግተዋቸዋል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚሰማው እያፈተለከ የሚገባውን ብቻ ነው::

እውጭ አገር የምንኖር ኢትዮጵያውያን አገር ውስጥ ካላችሁት ወገኖቻችን ጋር ፖለቲካ እንዳንወያይ ስልኩን መቆጣጠር ቢያቅታቸው ዋጋውን ወደላይ አንረውታል:: የትግራይ ወያኔዎች የሚያስከፍሉት ሌሎች አገሮች ከሚያስከፍሉት ጋራ ሲተያይ ልዩነቱ "ሰማይና ምድር" የሚባለው ዓይነት ነው:: በዚህ ዘዴያቸው አፋችንን ሊዘጉት ይሞክራሉ፤ ግን ገንዘብ ገፈፉን ብለን አንሸነፍላቸውም::

***አዲስ የጠላትነት መታወቂያ፤***

*የትግራይ ወያኔዎች ፋሺስትነት የመጀመሪያ መታወቂያ የመገናኛ ብዙኃኑን ለራሳቸው መጠቀሚያ ማድረጋቸው ነው:: አሁን ደግሞ፥ ተጨማሪ አዲስ የጠላትነት መታወቂያ አውጥተዋል፤ እሱውም ለሀገር ልማት እያሉ ለሙን መሬት ከገበሬው እየነጠቁ ለውጪ ሀብታም መቸርቸር ነው--ለሀገር ጥፋት ማለታቸው ነው:: አለማፈራቸው "የምንሸጠው ባዶውን መሬት ነው" ይላሉ:: መሬት ለምም ሆነ ጠፍ፥ ለሌላ ሀገር አይሸጥም:: አንድ የኢጣልያ ኩባንያ አሰብ አጠገብ በ1862 ዓ.ም. ትንሽ መሬት ከቦታው ሹም ላይ ከመግዛቱ በቀር እስከ ዛሬም ሆነ ከዚያ በፊት የኢትዮጵያ መሬት ለባዳ አልተሸጠም:: የኢጣልያ ኩባንያ የገዛው መሬት ለሀገሪቷ ምን ዓይነት መዘዝ እንዳስከተለ እንዳንረሳው ይኸው አብሮን ይኖራል:: ያም ሆነ ይህ፥ የትግራይ ወያኔዎች እንደሚሉት የሚሸጡት ባዶውን መሬት አይደለም:: እኔ በማገለግልበት ዩኒቨርስቲ የሚያገለግል ጋዜጠኛ በቪዲዮ የዘገበው መረጃ ገበሬዎቹ ከመሬታቸው ላይ እንደተባረሩ ሳይፈሩ ሲናገሩ ያሳያል:: ከዚህ የበለጠ ምን ይመጣብናል ብለው ይፍሩ? በማንም ሀገር መሬት ለውጪ ሀገር ሀብታም አይሸጥም:: ይኸ አገር በቀል ጠላት እንጂ ፋሺስቶችም የማያደርጉት ወንጀል ነው:: ፋሺስቶች ሕዝባቸውን የመናገርና የመጻፍ ነፃነት ይነፍጋሉ እንጂ ሀገራቸውን ለባዳ አይሸጡም::*

*የፋሽስትነት ሦስተኛው መታወቂያቸው ፓርቲያቸው አባላት ያሉት ለስሙ እንጂ ፈላጭ ቆራጫቸው መሪው ነው፤ የኢሕአዴግ አባላትም ማናቸውም ከመለስ ዜናዊ ቃል ዝንፍ ካለ፥ ቤቱ መቃብር፥ ዕድለኛም ከሆነ ቃሊቲ ወይም ዓለም በቃኝ እስር ቤት ነው:: ታዲያ አቶ መለስና አፈ-ቀላጢዎቹ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን አሠራር ሲነቅፉ፥ "ራሳቸውን እንኳን ማስተዳደር ሳይችሉ አገር እናስተዳደራለን ይላሉ፤ ብቃት ግን የላቸውም" ይሏቸዋል:: ድርጅቶቹን የሚነቅፏቸው ማናቸውንም ጉዳይ የሚወስኑት የዲሞክራሲን ሥርዓት ተከትለው ስለሆነ ነው:: በዲሞክራሲ ሥርዓት ሲወያዩ በሐሳብ መለያየት፥ መጋጨትም አለ:: ዲሞክራሲ በሰፈነበት አገር ሁሉ የሚታይ፥ ባልሰፈነበት ግን የማይታይ ነው:: እነመለስ እስቲ አንድ ቀን ትጥቃቸውን ይፍቱና ሲወያዩ እንይ! ብትንትናቸው ይወጣ ነበር::*

***የወያኔ ደጋፊዎች ሆይ፤***

*የወያኔ ደጋፊዎች ሆይ፤ የማንኛውም ብሔር ሰዎች ብትሆኑ፥ ምንም ቢሆን ሁላችሁም የነሱ ብጤዎች አይደላችሁም፤ ታዛቢ ሕሊናና ለኢትዮጵያ ልጅ ሕይወት ተቆርቋሪነት ከአለባችሁ፥ ነፍስና ሀገር ገዳይን ሲሆን ያጠፉታል፥ ካልሆነም ይሸሹታል እንጂ አይደግፉትም፥ አያጅቡትም:: ወያኔዎችን መደገፍ በተለይ በትግራይ ልጆች ላይ አያምርም:: ሲወርድ ሲዋረድ ከእኛ ዘመን የደረሰው መንግሥት የተወለደው ትግራይ ላይ ነው:: "እትግራይ ላይ የተወለደውን ብሔራዊ ክብር እትግራይ ላይ የተወለዱ ልጆች ገሠሡት፥ አጠፉት" ተብሎ እንዲመዘገብ አትፈልጉም::*

እናንተ ለኢትዮጵያ ህልውና ከማን አንሳችሁ ነው እንዲህ ስንጮህ እየሰማችሁን÷ የሚንዷትን የምትደግፉት?

እናንተ ለኢትዮጵያ ህልውና ከማን አንሳችሁ ነው አገር ሲጠፋ እኛ ስናለቅስ እናንተ የምታጨበጭቡት?

ኢትዮጵያ በገናናነቷ ብትኖር የእነማ ልጆች ከእናንተ ልጆች የበለጠ ይኩራባታል?

ኢትዮጵያ በገናናነቷ ብትኖር በእናንተና በልጆቻችሁ ላይ የሚደርሰው ጉዳት ምንድን ነው?

የጨቋኝ ገዢ ወገን መሆን ክብር የሚያስገኝ መስሏችሁ እንደሆን÷ ያ አስተሳሰብ አልፎ አሳፋሪነት ተተክቶበታል። ታሪካችሁ ተመዝግቦ ስለሚኖር የልጆቻችሁ ማፈሪያ አትሁኑ። ለራስም ለልጅም ክብር የሚያስገኘው÷ ሲሆን ከተገዢው ጋር ቆሞ ጨቋኙን ገዢ መታገል ካልሆነም ጨቋኝ ገዢን መራቅ ነው። ሕሊና ያላቸው ለሰው ልጅ ሁሉ ነፃነት ሲታገሉ÷ እናንተ ሕሊና እንደሌለው ከዘላቂ ወገን ይልቅ ጊዜያዊ ወገን ይብስብናል ብላችሁ ወገኖቻችሁን ኢትዮጵያውያንን ከሚጨቁኑ ጋር ወግናችኋል። የውገናችሁን ጥቅምና ጉዳት እንድታመዛዝኑት ላሳስባችሁ።

**ታይቶ የማይታወቅ ጠላትን ታይቶ የማይታወቅ የድል መምቻ ዘዴ፤**

ከላይ "ኢትዮጵያ . . . እንደዛሬው ያለ ጠላት ተነሥቶባት÷ እንደዛሬው ያለ የጠላት ማስወገጃ ዘዴ ገጥሚት አያውቅም" ብዬ ነበር። በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያን ወጥሮ የያዛት አዲሱ ዓይነት ጠላት ማን እንደሆን ካወቅን ከአዳዲስ ማስወገጃ ወይም ማሸነፊያ ዘዴዎች ስለ አንዱ አንድ ሁለት ቃላት ልናገር። እሱውም ከሦስት ቀን በኋላ የምታደርጉት ምርጫ ነው። ግን ምርጫ ሲባል በሰለጠኑት አገሮች እንደሚደረገው የምርጫውን ካርኒ ከምርጫው ሳጥን አስገብቶ ውጤቱን መጠበቅ አይደለም። እንደ ወያኔዎች ያሉ ጨቋኞች በሚገዙበት ሀገር የምርጫው ሳጥን የጦር መስክ ነው። ተወዳዳሪዎችና መራጮች የምርጫ ሳጥኑን ከመንግሥት አጭበርባሪዎች አተብቀው መጠበቅ ይኖርባቸዋል። ካልጠበቁት ዲክታተሮች እነሱን በሚደግፍ የምርጫ ካርኔ አስቀድመው ይሞሉታል። ከምርጫ በኋላም በድምፅ ቈጠራም ጊዜ ይሸውዳሉ፤ ወይም አጭበርብረው እውነተኛውን ሳጥን በውሸት ሳጥን ይለውጡታል። ወይም በድምፅ ቈጠራው ጊዜ የመንግሥት ደጋፊዎች ቍጥር ካነሰ ያበዙታል። ይኽ እንዳይሆን በብዛት ተሰብስባችሁ በአስፈሪ መልካችሁ መጠበቅ ይኖርባችኋል። እነእገሌ ይቈጣጠሩታል ብላችሁ ለነእገሌ አትተውላቸው።

አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባርንና ተለጣፊዎቹን እንደማይመርጡ ያለፈው ምርጫ ውጤት መስክሯል። እነሱ ግን በአሁኑ ምርጫ እንደሚያሸንፉ አምነዋል። ከዚያ ወዲህ ምን አዲስ ነገር ተፈጠረና ነው የሚፈለጉና በምርጫ የሚያሸንፉ የመሰላቸው? ጭቆናቸው እንደቀጠለ ነው፤ ጭከናቸውም በዚያው ልክ እንደቀጠለ ነው፤ ሰዉ የፈለገውን እንዳይመርጥ የሚያስፈራሩት ጓደኛውን እየደበደቡና እየገደሉ ነው። ሁለተኛው መተማመኛቸው የመራጮች ዳተኝነትና ተስፋ የመቍረጥ ስሜት ነው።

እንግዲህ ሕዝቡ እነዚህን ከሓዲዎች በሰላምና በጤና ሊያሰናብታቸው ከወሰነ÷ ድል ለማግኘት የትግል አቅዱን ከላይ እንዳልኩት በጥንቃቄ÷ በንቃትና በትጋት እያሰናዳ ነው ወይስ አይደለም? ሕዝቡ የሚያባርራቸው÷ የዘረኝነት አገዛዛቸው ከቤተ መንግሥት ተነቅሎ በቦታው ሁሉን የሚያቅፍ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲተከል ነው። ሕዝቡ ዓላማው ይህ ከሆነ÷ እምነት የጣለበትን ፓርቲ በድምፁ ኀይል ስልጣን ለማስያዝ ሳይውል ሳያድር÷ ጊዜው ሳያልፍ አሁኑኑ መዘጋጀት ይኖርበታል።

ካልተዘጋጀ፥ ጩኸቱና ሆታው ከምኞት የማያልፍ፥ ከንቱ የመረዋ ድምፅ ሆኖ ይቀራል። ብዙ ፓርቲዎች ለመወዳደር ተመዝግበዋል። እጩዎቻቸውንም አስሰልፈዋል። ተቃዋሚውን የሚመርጠው ድምፅ በቡድኖቹ ልክ ከተከፋፈለ፥ የትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር የመሠረተው የትግራይ ወያኔ ግዛት መሰነባበቻ ዘመን አይመጣም። እርግጥ፥ ፓርቲዎች ተባብረው በአንድነት በትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር ላይ ቢዘምቱበት ድሉ አስተማማኝ ይሆናል። ሆኖም፥ እነሱ በፈቃዳቸው ቢተባበሩም ባይተባበሩም፥ ሕዝብ ድምፁን የማሸነፍ ተስፋ ላለው ፓርቲ ብቻ በመስጠት ሊያስተባብራቸው ይችላል። ድምፅ አታባክኑ፤ የተበታተነ ድምፅ ወያኔዎችን ለዘላለም ያኖራል እንጂ አያሰናብትም። ለማንኛውም፥ አንድ መራጭ በምንም ምክንያት የኢሕአዴግን ተወዳዳሪዎች ከመረጠ በእናቱ በኢትዮጵያ ላይ የሞት ፍርድ መፍረዱን ይወቅ። አንድ ልጅ በአሳደገችውና በታሪኳ በአኮራችው እናቱ ላይ የሞት ፍርድ የሚፈርደው ምን ምክንያት ቢኖረው ነው? እናትን ከመግደል መሞት ይሻላል። ከላይ እንደተናገርኩት፥ የኢሕአዴግን ተወዳዳሪዎች ከመምረጥ አንድ ተላላፊ መንገደኛ መምረጥ ይሻላል።

ባለፈው የ1997 ምርጫ ቅንጅት አሸንፎ እንደነበረ ዓለም መስክሯል። ግን የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር ወታደሩና ፖሊሱ በቊጥጥሩ ስር ስለሆነ፥ ራሱን አሸናፊ፥ ቅንጅትን ተሸናፊ አድርጎ ስልጣኑን እንደያዘ ቀረ። ይህ ሁኔታ ያደረሰው ጉዳት ከግምት በላይ ነው። ድምፅ የመነጠቁን ጉዳት ለጊዜው ብናልፈውም፥ ይበልጥ የሚያሠጋው በዚህ ከሦስት ቀን በኋላ በሚደረገው ምርጫ ላይ ሊያደርግ የሚችለው አፍራሽ ተጽዕኖ ነው። ብዙ ሰዎች፥ “ከምርጫው ጣቢያ ለመድረስ ረጅም መንገድ ሄደን፥ ከደረስንም በኋላ ተራችን እስኪደርስ ቀኑን ሙሉ በፀሓይ ስንንቃቃ ውለን፥ ያደረግነው ምርጫ ያተረፈልን ከሥራ መባረር፥ እንደወንጀለኛ እስራትና ዱላ ብቻ ነው። በመብታችን ብንጠቀም ያን ሁሉ ሥቃይ ያሳዩን የትግራይ ወያኔዎች ዛሬም የትናንቶቹ ናቸው። ካለፈው የማይማር ሞኝ ብቻ ነው። የ97ቱ ተመክሮ ያላስተማረን ይመስል፥ የሆነውን ሁሉ ዘንድሮ በ2002 እንደግመውም” ሲሉ ተሰምተዋል።

አይፈረድባቸውም። ግን እነዚህ ቃላት ለትግራይ ወያኔዎች እጅግ ታላቅ ብሥራት ያዘሉ ናቸው። ሆኖም፥ የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር አባላት ይህን የሕዝብ ተስፋ መቊረጥ በመተማመን፥ የምርጫ ሥነ ምግባር የተባለውን ውል በመፈረም ራሳቸውን ከግዴታ አስገብተዋል። በፊት በር ለመውጣት የሚያስቸግራቸው ውል ነው። ከግዴታ ያስገባቸው በአንድ በኩል ለነፃነት በጀግንነት ሲታገሉ የፈሰሰው የቅንጅት አባላት ደም እንደአቤል ደም ወደ እግዚአብሔር ስለጮኸና በሌላ በኩል ደግሞ እርዳታ እየሰጡ ወያኔዎችን በስልጣን ላይ እንዲቆዩ ያደረጉት የውጪ አገር መንግሥታት ናቸው።

የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር የተማመነው የሕዝብን ተስፋ መቊረጥ መሆኑ እየተነገረው፥ ተስፋ በመቊረጥ፥ በምርጫው ላለመሳተፍ የወሰነ ሰው ካለ፥ አገሩን እንደሸጠ፥ ራሱን ጨምሮ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለባርነት እንደዳረገው ይወቅ። ለነፃነት መታገልን ምንም ክፉ ነገር አያሰናክለውም። አባቶቻችን ነፃነታችንን ያቆዩልን እየገደሉ ብቻ ሳይሆን እየሞቱም ነው።

ተስፋ መቊረጥ፥ ለጠላት መሸነፍ ነው።

ተስፋ መቊረጥ፥ “አገር ሲጠፋ መቸስ በሀገር የመጣ ነው፤ ምን ማድረግ ይቻላል” ብሎ ፋይዳ ቢስ ከንፈር መምጠጥ ነው።

ተስፋ መቊረጥ፥ የሀገሪቱ ሀብት ሕዝቧን አጥግቦ ለሌሎች ሊተርፍ ሲችል በችጋር ማለቅን ያመጣል።

ተስፋ መቊረጥ፥ ሥራ ባልጠፋበት ሀገር ሥራ አጥቶ ሲንከራተቱ መዋልን ያስከትላል።

ተስፋ መቍረጥ፥ በራስ ሀገር ተዋርዶ መኖርን እንዲቀበሉ ያደርጋል።

ተስፋ መቍረጥ፥ ውጤቱ ኢትዮጵያን የመሰለች ሀገር ያላቸው ሰዎች በሰው ሀገር እየተንከራተቱ የትም ሲወድቁ የሚደርስላቸው አምባሳደር ከማጣት ያደርሳል።

የተስፋ መቍረጥ ምስጢሩ፥ ተስፋ አስቈራጩን ለማባረር ሲቻል ለማባረር ታጥቆ አለመነሣት ነው። ታጥቆ ከተነሡ የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር በሺ የሚቈጠር ወታደር ይዞ በሚሊዮን የሚቈጠር ሕዝብ ሊጨቁን አይችልም። ዘመኑ ተለውጧል፤ ብዙ የትግል ዘዴዎችም ተገኝተዋል። ሁሉንም በጊዜያቸው እንነጋገርባቸዋለን። አሁን ጊዜው ከሦስት ቀን በኋላ የሚካሄደው ምርጫ ስለሆነ ስለሱ እንወያይ።

በአለፈው ምርጫ የሆነውን እያስታወስን፥ የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር በምርጫ ስልጣን አይለቁም ማለትን ለጊዜው እንተወው። አይሆንምን ትተን ይሆናልን እንያዝ። አይሆንም ካልን የሚሆነው አንድ ነገር ብቻ ነው፤ የትግሬ ወያኔዎች ከጥቂት ተመዝጋቢዎች ጋር ተወዳድረው ሳንቲም ከጣሉላቸው መራጮች የሚያገኙትን ድምፅ ሰባስበው ያሸንፋሉ። ያሸነፈን "እንኳን ደስ ያለህ" ማለት ስለሚገባ የደስታ መልእክት ከሚያስተላልፉት መካከል አታድርጉን። እነሱም ለሞኙ የጣልንለትን "አሹቁን ሲያወልቅ፥ ይዣት ውልቅ" እያሉ በቡልጋ ዘፈን ያሾፉብናል።

ይሆናል ብለን ከታገልን ግን ውጤቱ ከሦስት አንዱ ይሆናል፤ ወይ እናሸንፋለን፥ ወይ እንሸነፋለን፥ ወይ የትግሬ ወያኔዎች ያጭበረብራሉ። ያጭበረብራሉ ብሎ አለመምረጥ ከሦስት አንዱ ሊሆን የሚችለውን የማሸነፍ ዕድልን መዝጋት ነው። ሊያጭበረብሩ፥ ምናልባት በንጹሕና በሰላማዊ ሰው ላይ ጉዳት ሊያመጡ ይችሉ ይሆናል። ግን የሚደርሰው ጉዳት ለነፃነት ከሚደረገው ትግል አንጻር ሲታይ ላለመምረጥ ምክንያት አይሆንም። አርቆ የሚያይ ኢትዮጵያዊ በትግል ጊዜ የሚደርሰውን ጉዳት ፈርቶ አያፈገፍግም። አለዚያማ "የአባቶቼን ታሪክ አታሳዩኝ፥ አታሰሙኝ፥ አታስነብቡኝ" ሊል ነው። ትግሉ ይቀጥላል፤ የሀገርና የነፃነት ጉዳይ ስለሆነ ሌሎቹን የትግል ዘዴዎችና ስልቶች ይዘን እንቀጥላለን። የመላ ኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያቅፍ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ሳይቋቋም ነፃና ኩሩ ሕዝብ ለዓይኑ እንቅልፍ ለቅንድቡ ዕረፍት አያሳይም።

ማንን ለመምረጥ?

ሰው ከጠፋ አንዱን መንገደኛም ቢሆን ጠልፋችሁ ምረጡት እንጂ የኢሕአዴግን እጩኛ እንዳትመርጡ። ለማንኛውምሕዝቡ የትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባርን ለማሰናበት የሚፈልገው በሀገሪቱና በሕዝቡ ላይ ያመጡትን በደል በሚያስወግድ ቡድን ለመተካት ነው። ሕዝቡ በደል የሚላቸው ከዚህ በታች ለምሳሌ ያህል የተዘረዘሩትን ብሔራዊ ወንጀሎች ነው።

የትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር ሰዎች የኤርትራን ሕዝብ ሳይበድሉ ለኢትዮጵያ የባሕር ወደቧን ማስቀረት ሲቻላቸው ሀገሪቷን በመጥላት ብቻ ያለወደብ አስቀሯት፤

የትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር ሰዎች ኢትዮጵያን የባሕር ወደብ ለማሳጣት ሲሉ ከሻዕቢያ ጋር በሀገሪቱ አንድነት ላይ ዘመቱባት፤

ማንንም ሳይበድሉ የሕዝቡን አንድነት መጠበቅ ሲቻላቸው፥ ሕዝቡን በመጥላት ብቻ "የተለያየ ቋንቋ ከተነጋገርክ የተለያየህ ሕዝብ ነህና ሚናህን በቋንቋህ ለይ" የሚል መርዝ ረጨባት።

ማንንም ሳይበድሉ ሕዝቡ የፈለገውን ዓይነት መንግሥት እንዲያቋቁም መፍቀድ ሲቻላቸው፥ ሕዝቡን በመጥላታቸው የዲሞክራሲ አስተዳደር ነፈጉት። ታሪኩን ወደኋላ በመጎተት የትግራይ ስርወ መንግሥት ዘረጉበት።

ማንንም ሳይበድሉ ሕዝቡን ከረኀብ፥ ከበሽታ፥ ከአለመማር ማላቀቅ ሲቻላቸው፥ በጥላቻ እየተገፉ ብሔራዊ ኀላፊነታቸውንና ግዴታቸውን ለግል ጥቅማቸው አዋሉት።

ማንንም ሳይበድሉ ሕዝቡን በፈቃዱ ካልታረሰ መሬት ላይ ለግብርና ማስፈር ሲቻላቸው፥ ሀገሪቷን (በተለየም አማራን) በመጥላት ብቻ ዓለም ጉድ እስኪል መሬቱን በፔትሮ-ዶላር ቸበቸቡት፤ ከሀገር ወጥቶ የሌሎች አሽከሮች ሊያደርጓቸው ያልቻሉትን እዚሁ ባሉበት አሽከሮች እንዲሆኑ ጌቶች ከዓረብ፥ ከህንድ፥ ከፓኪስታን እደጃፋቸው ድረስ አመጡላቸው።

ማንንም ሳይበድሉ በምዕራብ በኩል ያለውን ለም መሬት መጠበቅ ሲቻላቸው፥ ሀገሪቷን በመጥላት ብቻ የሰፈረበትን የኢትዮጵያ ሕዝብ አፈናቅለው ለሱዳን ሰጡት። ማኅበረ ሥላሴ የሚባለው ገዳምም የሱዳን ዜጋ ሊሆን ነው።

ማንንም ሳይበድሉ ሕዝቡ እንዳንድ ሕዝብ በሰላም መበፈቃቀር እንዲኖር ማድረግ ሲቻላቸው፥ ሀገሪቷን በመጥላት ብቻ በሬዲዮና በቴሌቪዥን በሚረጩት የጥላቻ መርዝ ሊያጣሉት ይሞክራሉ። አንዳንድ ቦታ ቀንቷቸዋል።

ማንንም ሳይበድሉ የሀገሪቱን ታሪክ መንከባከብ ሲችሉ ሕዝቡን በመጥላት ብቻ ኢትዮጵያ የመቶ ዓመት ሕፃን ነች የሚል መርዝ ይረጫሉ።

**የጨረባ ተዝካር፤**

የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲህ ያለ ወንጀለኛን ይመርጣል ማለት ዘበት ነው። "ስድስት ወር ብቻ" ማለቱ ስለዚህ ነው። ሆኖም በክርክሩ ጊዜ የሚሰማው ጩኸቱን ቀሙኝ ዓይነት ነው። ወያኔዎች ሀገርቷን እያጠፉ፥ ከእነሱ የበለጠ ለሀገሪቷ አንድነት፥ ለታሪኳ ተቆርቋሪነት ማንም እንደሌለ ሲናገሩ ነበር። ሕዝቡ ሊያሰናብታቸው ታጥቆ መነሣቱን የሰሙ አይመስሉም።

ግን ሕዝቡ የትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር ሰዎችን ሊያሰናብት የሚፈልገው እነዚህንና ሌሎቹን በደሎች በሚያስወግድ፥ የሀገሪቷን ክብር በሚመልስና እርቅ ማውረድ በሚችል ቡድን ለመተካት ነው። ከሦስት ቀን በኋላ በሚፈጸመው ምርጫ ለመወዳደር ከተሰለፉት የፖለቲካ ቡድኖች ውስጥ ይኸንን ሁኔታ የሚያሟላና የማሸነፍ ዕድል ያለው የትኛው እንደሆነ ሕዝቡ ከራሱ ተመክሮ እንደሚያውቅ ተስፋ አደርጋለሁ። የተደረጉት ክርክሮች ግን ሁሉም የጨረባ ተዝካር ይመስሉ ነበር። ያ ሁሉ ሕዝብ በፓርቲ ስም ተሰብስቦ የሚናገረው አንድ ዓይነት ስለነበረ መራጩን ያወናብዳል እንጂ አይረዳውም። ከአንድ ወያኔ ስልጣን ለመውሰድ ብዙ ሰው ከተሰለፈ የቁማር ጨዋታ ይሆናል። በየትም ሀገር የምርጫው ጊዜ እንዲህ ቀርቦ እያለ የፓርቲዎች መንጋ ሲከራከሩ ታይተው አይታወቅም። ይህ ሁሉ መወናበድ የተፈጠረው አከራካሪው፥ ማለትም የቁማሩ ባለቤት፥ ራሱ ወያኔ ስለሆነ ነው፤ በሌሎች አገሮች እንደሚደረገው አከራካሪው ለሀገር ተቆርቋሪ ገለልተኛ አካል ቢሆን ኖሮ ከሦስት የማይበልጡ ቡድኖችን ብቻ መርጦ ያከራክር ነበር። የቁማር ቤት ባለቤት ያከስራል እንጂ አይከስርም።

ለመሆኑ የትግሬዎቹ ቡድን በድምፅ ብልጫ ቢሸነፍ ሽንፈቱን በጸጋ ተቀብሎ የተደላደለበትን ቤተ መንግሥት በሰላም ይለቃል ወይ? ምንም በተአምራት ባምን አቶ መለስ ኢትዮጵያን የመጥላት በሽታው ሳይለቀው በጤናው "አገሪቱን መልሶ ለአማራ"

አይለቅም። አማራ ስል እንዳትሳሳቱ እሱና እሱን የመሰሉ ሰዎች አማራ የሚሉት ከላይ የዘረዘርኳቸውን እኩይ ሥራዎቹን የሚቃወመውን ሁሉ ነው። በነሱ ዘንድ “አንድ ሀገር፥ አንድ ሕዝብ፥ አንድ ባንዲራ፥ ለአንድ ሰው አንድ ድምፅ” የሚል ሁሉ ወንጀለኛ አማራ ነው። በነሱ ዘንድ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባኤ የአማራ ድርጅት ነው። በነሱ ዘንድ ቅንጅት በጉራጌዎች የተደገፈ የአማራ ድርጅት ነበር። መለከት ኢትዮጵያ ሬዲዮም የኢትዮጵያን አንድነትና ሉዓላዊነት የሕዝብን እኩልነት ዓላማው ስላደረገ፥ የትግሬዎቹ ቡድን የአማራ ሬዲዮ ጣቢያ ቢለው ወይም የአንድ ፓርቲ ደጋፊ ቢያደርገው አይገርመንም። እውነታው ግን ጣቢያው እርዳታ የሚያገኘው የአንድ የተለየ ፓርቲ እንዳይሆን ቃል የገባውን ካመኑ የተለያየ ፓርቲ ደጋፊዎች ነው።

ወደ ትግራይ ነፃ አውጪ ድርጅት ልመለስና ይህ መሠርይ ድርጅት የሀገሪቱ አንድነት ሲነሣ የሚያንቀጠቀጠው በሽታው ሳይለቀው ሽንፈትን በቀላሉ አይቀበልም። ግን በሀገር ውስጥ ያሉት ፓርቲዎች ለመወዳደር ወስነዋል። ዓለምም የምርጫውን ሂደት እየተከታተለ ነው። ወያኔዎች የምርጫውን ውጤት ለመቀበል የሚያስገድዳቸው ሁኔታ ተፈጥሯል ማለት ነው። ውጤቱን ለመቀበል ከአቅማሙም እንዲቀበሉ ማስገደድ የሕዝብ ግዴታ ነው። ሁኔታው ይህ ከሆነ፥ ተቃዋሚዎች ከምርጫው ለመግባት ያደረጉትን ውሳኔ መደገፍና የሚቻለውን ያህል መርዳት፥ ከሁሉም ይልቅ ለመምረጥ መዘጋጀት ብሔራዊ ግዴታችን ነው።

ወያኔዎች ምርጫውን ለማሸነፍ የተማመኑበት ሌላው ነገር ማስፈራራት ነው። “ኢትዮጵያውያን ፈሪዎች ስለሆኑ፥ በማስፈራራት እኛን እንዲመርጡ እናደርጋቸዋለን” የሚል እምነት አላቸው። እምነታቸው እንዲይዝላቸው በቃል ከማስፈራራት አንሥቶ እስከመግደል ድረስ የማይሠሩት ወንጀል የለም። ኢትዮጵያውያንን አያውቋቸውም ማለት ነው። ኢትዮጵያውያን በሀገራቸው፥ በሃይማኖታቸው፥ በቤተሰባቸው ለሚመጣባቸው በፍርሃት እንደማይሸነፉለት በታሪክ አስመስክረዋል። አሁንም እንደገና እናስመሰክራለን።

**በምርጫው መሳተፍ ተገቢ ነው?**

ይኸንን ጥያቄ የማንሣት ዘመን አልፏል። ተወስኗል፤ ማፈግፈግ አይገባም። እርፍ ይዞ ወደኋላ የሚያይ ገበሬ ሰብሉ አይሠምርለትም። አቶ መለስ የሚወዳደረው ባይኖር ደስታውን አይችለውም። የነፃነት ጉዳይ ነው። እንደ አፍጋኒስታኑ መሪ የሚወዳደረው አጥቶ ብቻውን ሮጦ ከሚያሸንፍ፥ አጭበርብሮ አሸነፍኩ ቢል ይሻለናል። አለዚያማ ምን ይዘን እናቄስለዋለን? ባለፈው ምርጫ በማጭበርበሩ የቱን ያህል እንደቄሰለ ቀስ እያለ ተሰምቷል። እሱም አውቆት አሁን በቀጥታ ለማሸነፍ ወይም በዘዴ ለማጭበርበር ተዘጋጅቷል። ግን ከሦስት ቀን በኋላ ድባቅ ሲመታ ይታየናል። መኢአድና መድረክ በመቀሌና በአዲስ አበባ፥ መኢአድ በባሕር ዳርና በሆሳዕና ያካሄዱትን ቅስቀሳ ስናይ፥ የነፃነት ጮራ ይታየናል።

ከጮራ በኋላ የሚመጣው ሙሉ ብርሃን ነው፤ ፓርቲዎቹ ጮራውን አሳይተውናል፤ በምርጫችሁ ሙሉውን ብርሃን አሳዩን። “ሌሎችን ብትመርጧቸው አገሪቷን ወደኋላ ይጎትቷታል” የሚለውን የወያኔ ፕሮፓጋንዳ አትመኑ፤ ወደዲሞክራሲ አስተዳደር ያደረግነውን እርምጃ ወደኋላ የጎተተስ እነሱ ናቸው። በፈጣኑ እርምጃችን እነሱ ደንቃራ ባይሆኑብን ኖሮ ዛሬ ከራሳችን አልፈን ለሌሎች እንተርፍ ነበር። በቁጭት ከተነሣን፥ ወያኔ የነሣንን ዲሞክራሲና እድገት ወያኔን ያባረራችሁ ማግስት እናገኘዋለን። ከሦስት ቀን በኋላ **በሚደረገው ምርጫ ለመሳተፍ ተዘጋጁ፤ ተዘጋጁ፤ ተዘጋጁ። መሰናበቻ መሰናበቻ፥ ሦስት ቀን ብቻ።**